ምዕራፍ ፪
ሥነ ፍጥረት

Chapter 2
Creation

ምዕራፍ ፪ ሥነ ፍጥረት

- ቅዱስ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን መኖር በማረጋገጥ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ በማለት ይጀምራል። (ዘፍ፡፩፡፩)
    - ቅድስ ጳውሎስም በዕብራውያን መልእክቱ ፫፡፬ ላይ “ሁሉን የፈጠረ (ያዘጋጀ) እግዚአብሔር ነው” ይላል።
- እግዚአብሔር ሁሉን አስገኘ፥ ለሁሉ ለነገር መገኛ ጥንትና መሠረት ነው።
    - ለእርሱ ግን ለህላዌው ምክንያት የለውም።
    - (የሐዋርያት ፀሎተ ሃይማኖት) እግዚአብሔር ይህን የሚታየውንና የማይታየውን ዓለም በውስጣቸውም ያሉትን ሁሉ ከቸርነቱ ብዛት የተነሣ ፈጠረ።
    - (ኢሳ.፵፪፡፭)።

Chapter 2 Creation

- The Holy Scripture begins with “God created heaven and earth ascertaining the existence of God,” (Gen.1:1).
    - St. Paul also said “the builder of all things God” (Heb.3:4).

- እግዚአብሔር ይህን ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር ያስገኘው “ለይኩን” ባለው ቃሉ ብቻ ነው። ይህ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ምንም ነገር አልነበረምና
  - ጥበበ ሰሎሞን ፲፩፡፲፯፤
  - ፩ መቃብ ፳፯፡፩
  - ቅዱስ ጳውሎስም “ዓለሞች ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈጠሩ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናስተውላለን” (ዕብ ፲፩፡፫) በማለት እግዚአብሔር ፍጥረትን ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ መፍጠሩን አስረድቷል።

- God brought the world out of nothing into being by his word. He said, “Let it be!”. There was nothing before the creation of the world.
  - Wis.11:17;
  - 1 Maccab. 27:1.
  - St. Paul explained that God created the world out of nothing when he said “By the faith we understand that the world was created by the word of God, so that what is seen was made out of things which do not appear”. (Heb.11:3).

ምዕራፍ ፪ ሥነ ፍጥረት (የቀጠለ....

- ፈጣሪ ፍጥረታት እግዚአብሔር ሥነ ፍጥረትን በየመልኩና በየወገኑ መፍጠሩ
  - ክብሩ ይገለጥበትና ስሙ ይቀደስበት ነው።
  - ይህም ነብዩ ኢሳይያስ “ፍጥረታትን ሁሉ ለክብሬ ፈጠርኋቸው አለ እግዚአብሔር” ብሎ ተናግሮአል። (ኢሳ. ፵፫፡፯)
- ፍጥረታት ሁሉ በየወገናቸው
  - ከዕለተ እሑድ እስከ ዕለተ ዓርብ ባሉት ስድስት ቀናት በቅደም ተከተል መፈጠራቸውን ቅዱስ መጽሐፍ ይናገራል።
- እነዚህም በስድስቱ ዕለታት የተፈጠሩ ፍጥረታት በየወገን በየወገናቸው ተቆጥረው
  - ሃያ ሁለት መሆናቸውን መጽሐፈ ኩፋሌ ይናገራል። (ዘፍ.፩፡፩-፴፩፤ ኩፋሌ ፫፡፱)

Chapter 2 Creation (cont …

- God created all and everything after their own kinds for
  - His glory so that His power shall be glorified and his name be hallowed.
  - Isaiah the prophet quoted the word of God by saying, “…everyone who is called by my name, whom I created for my glory, whom I formed and made.” (Isa.43:7).
- The Holy Scripture makes it clear that all the creations were created in six days after their own kinds – Sunday to Friday.
- Numerically, these creations are divided into
  - Twenty-two groups. (Gen.1:31; Jubliee 3:9)

በየዕለቱ የተፈጠሩት ፍጥረታትም በሚከተለው ሁኔታ የተገለጡ ናቸው።

ሀ) <u>የእሑድ ፍጥረታት</u>

፩. እሳት
፪. ነፍስ
፫. ውሃ
፬. መሬት

} ዐራቱ ባሕርያት

፭. ጨለማ
፮. ሰባቱ ሰማያት
፯. መላእክት
፰. ብርሃን ናቸው። (ኩፋሌ ፪፡፭-፰፤ ዘፍ. ፩፡፩-፭)

The creations of each day are the following.

A.<u>The first day – Sunday</u>

1.Fire
2.Wind
3.Water
4.Earth

} **The four elements**

5.Darkness
6.The seven heavens
7.Angles
8.Light (Jubilee 2:5-8; Gen. 1:1-5)

ለ) **የሰኞ ፍጥረታት**

በምድር ላይ ሞልቶ የነበረው ውሃ ተከፍሎ ጠፈር ተገለጠ (ዘፍ. ፩፡፮-፰፤ ኩፋሌ ፪፡፱፤ ዘፍ.፩፡፱)

ሐ) **የማክሰኞ ፍጥረታት**

፩. በጣት የሚለቀሙ አትክልት

፪. በማጭድ የሚታጨዱ አዝርዕት

፫. በምላር የሚቆረጡ ዕፀዋት ናቸው። (ዘፍ.፩፡፲፩-፲፪)

B. The second day – Monday

The water that covered the earth were divided and the firmament in the midst of the waters appeared . (Gen. 1:6-9, Jubilee 2:9)

C. The third day – Tuesday

1. Vegetation that can be plucked with figures
2. Plants (grasses) that can be cut with sickle
3. Trees that can be cut with axe (Gen 1:11-13)

መ) <u>የረቡዕ ፍጥረታት</u>

፩. ፀሐይ

፪. ጨረቃ

፫. ከዋክብት ናቸው። (ዘፍ. ፩፡፲፬-፲፮)

ሠ) <u>የሐሙስ ፍጥረታት</u>

በደመ ነፍስ የሚንቃሳቀሱ ከባሕር ውስጥ

፩. በደረት የሚሳቡ

፪. በእግር የሚያኮበኩቡ

፫. በክንፍ የሚበሩ እንስሳት፥ አራዊትና አዕዋፍ ናቸው። (ዘፍ. ፩፡፳-፳፪)

D. <u>The fourth day – Wednesday</u>

1. The sun
2. The moon
3. The stars (Gen 1:14-16)

E. <u>The fifth day – Thursday</u>

In the water

1. Those creeping with their breastbone (chest)
2. Creatures moving with their feet
3. The flying birds, animals and beasts (Gen 1:20-22)

ረ) <u>የዐርብ ፍጥረታት</u>

በደመ ነፍስ ሕይወት የሚንቀሳቀሱ በየብስ የሚኖሩ፥

፩. ዘመደ እንሰሳ

፪. ዘመደ አዕዋፍ

፫. ዘመደ አራዊት

፬. በነባቢት ነፍስ የሚንቃሳቀሱ ናቸው። (ዘፍ.፩፡፳፬-፳፰)

እነዚህን ሁሉ ፍጥረታት በየወገኑ ከፈጠራቸው በኋላ መልካም እንደሆኑ አይቶ እግዚአብሔር በሥራው ደስ አለው እንዲበዙም ባረካቸው። (ዘፍ. ፩፡፳፩፤ መዝ. ፻፫፡፴፩)

F. <u>The six day – Friday</u>

On dry land

1. Animals
2. Birds and fowls
3. Beasts of the earth
4. Man with a living soul

God, after creating all these creations after their own kind saw that everything was good. He was satisfied and blessed them to be fruitful and multiply in order for their continuance. (Gen. 1:21; Ps. 104:31)

የሰው ተፈጥሮ

እግዚአብሔር ከዕለተ እሑድ እስከ ዕለተ ዐርብ ያሉ ፍጥረታትን በየዓይነታቸው ከፈጠረ ብኋላ

- ሰውን የእነዚህ ሁሉ የበላይ ገዢ አድርጎ
- በመልኩና በአረያው ፈጠረው፥
- በደመ ነፍስ ሕይወት ከሚኖሩ ፍጥረታት የምትለየውን ነባቢት፥ ለባዊትና ሕያውት ነፍስን በውስጡ አስደረበት።
- ወንድና ሴትም አደረጋቸው
- "ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት ግዙአትም" ብሎ ባረካጸው። (ዘፍ. ፩፡፳፮-፳፰)።
- በእግዚአብሔር አረያን ምሳሌ የተፈጠርው ሰው ባለ አእምሮ ፍጡር ነው።

Creation of Man

After God created all the numerous creatures according to their kind, from Sunday to Friday,

- He made man in His own image and after His likeness,
- To be the superior and have dominion over all other creatures.
- Man was made in a more distinct manner. God breathed into his nostril the breath of life, which distinguishes him from all other creatures which live and act on instinct.
- God created them male and female and blessed them to be fruitful and multiply and replenish the earth and subdue it. (Gen. 1:26-28).
- Man who is made in the image of God is rational.

ሰ) ፯ኛ ቀን፡-

- እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ከመፍጠር ሥራው ዐረፈ።
- ስለዚህ ሰባተናይቱን ቀን የዕረፈት ቀን እንድትሆን ባራካት ቀደሳትም ተብሎ ተጻፈ። (ዘፍ.፪፡፫)
- ስለዚህ እግዚአብሔር የፍጥረታት ሁሉ አስገኝና ባለቤት ነው።
- እግዚአብሔር ዓለምን በሥልጣኑ ማስገኘት ብቻ ሳይሆን መጋቢው፥ መሪውና ጠባቂውም ነው።
    - (መዝ. ፻፫፡፳፯-፴፩፤ ፩ቆሮ. ፫፡፳፪፣ ፲፭፡፳፰፤ የሐዋ. ፲፬፡፲፯)

G. Seventh Day

- God ceased from all works of creation and rested on the seventh day.
- He blessed and hallowed the seventh day to be observed as a rest and a holy day. (Gen. 2:3)
- God is the Creator and Giver of Life and sustains
- His Providence, protects and guides all that He created
    - (Ps. 104:27-31; 1Cor.3:22, 15:28; Acts 14:17)